# ዛሬ ባህርዳር ላይ ስብሰባ የጠራው ግንቦት 7 ነው። መሳሪያ ይዘው በመውጣትም ተቃውሞ ያደረጉት የግንቦት 7 ወታደሮች የነበሩ ናቸው

March 24, 2019

## ውብሸት ሙላት

የግንቦት 7 ወታደሮች ወረታ ካምፕ ውስጥ ተጥለው ለከፍተኛ ችግር መጋለጣቸው ይታወቃል። ፐ/ር ብርሃኑ ነጋም ባህር ዳር ብዙ ጊዜ ቢሄዱም ወረታ በመሄድ የወታደሮቹን ችግር ለመፍታት፣ያለምንም ዓይነት ሥራ እንዲቀመጡ የተደረጉትን፣ ጥረት ማድረግ ይገባቸው ነበር።

የኦነግ፣ የኦብነግ፣ የአድኃን፣ የአርበኞች ግንባር ወታደሮችን ክልሎቹ የተቀበሏቸው ሲሆን የግንቦት 7 ን ግን የፌደራል መንግሥት እንዲረከባቸው እነ ፐ/ር ብርሃኑና አንዳርጋቸው ጽጌ ማድረግ ይጠበቅባቸው ነበር።

ይህን ባለማድረጋቸው የተቀየሙ ወታደሮች መሳሪያ ይዘው ቢመጡ በዋናነት መወቀስ ያለበት ራሱ ግንቦት 7 ነው። ለዚያም ይመስላል ወደ ወረታ ያቀኑት። በግንቦት 7 ከፍተኛ አመራሮች እንደተካዱ የቆጠሩት ወታደሮች ድርጊት አሁንም በድጋሚ መወቀስ ያለበት ግንቦት 7 ነው።

ከዚያ ውጭ ያው የሰልፍ አደራረግ ሕግ (ሰልፍ ሲደረግ በሕግ መሟላት ያለባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላትን በሚመለከት ሳይዛነፉ አሟልቶ) የሚጠይቀውን መስፈርት ማሟላት፣ መጣስ በፍጹም የለበትም

https://www.satenaw.com/amharic/archives/65531